አማኑኤል ደርሶ

# መልስ

## ምዕራፍ ፩ ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ታሪኬን ፡ የማጫውታችሁ ፡ ይቅርታ ፡ ለመጠየቅ ፡ አለመሆኑን ፡ ልታውቁልኝ ፡ እወዳለሁ ። የማን ፡ ይቅርታ ? የምን ፡ ይቅርታ ? ይቅርታ ፡ መጠየቅስ ፡ የራስን ፡ ሕሊና ፡ ነው ። ሰው ፡ ከሕሊናው ፡ ጋር ፡ ከታረቀ ፡ ሌላው ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። ከአብዛኛው ፡ ባልሻልም ፤ ከአብዛኛው ፡ የባስኩ ፡ አይደለሁም ። በኔ ፡ ዓይን ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ጋሬጣ ፡ ከሌላው ፡ እንደማይበልጥ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ሁሉም ፡ ጠፍቷል ። እኔም ፡ «ከጠፋው ፡ ትውልድ ፡» አንዱ ፡ ግለሰብ ፡ ነኝ ። ስለዚህም ፡ ታሪኬ ፡ «ስለጠፋው ፡ ትውልድ» ፡ ደህና ፡ ሥዕል ፡ እንደሚሰጥ ፡ አምናለሁ ። በዝርዝር ፡ ለመተረክ ፡ የፈለግሁበት አንዱ ፡ ምክንያት ፡ ይኸው ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ ይቅርታ ፡ ልጠይቀው፡ የሚገባ፡ ፍጡር ፡ ቢኖር፡ ፈጽሜአለሁ።

ታሪኬን ፡ በዝርዝር ፡ አንድ ፡ ጊዜ፤ ለመናገር ፡ የፈለግሁበት ፡ አንዱ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ዘወትር ፡ መጻፍ ፡ ስላሰለቸኝ ፡ ነው ። እንደጠንቋይ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ፡ ስጫንቁር ፡ መዋል ፡ አለብኝ ። ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በየዕለቱ ፡ አንድ ፡ ማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ እጨርሳለሁ ። «እህ ፡ አየለ ፡ እንዴት ፡ ነበር ? እስኪ ፡ ንገረን ? » « ያን ፡ ሁሉ ገንዘብ ፡ እንዴት ፡ ጨረስከው ? » «አሁን ፡ ምን ፡ ይሰ

## ምዕራፍ ፡ ፲ ፡

በበነጋው ፡ ሥራ ፡ አልገባሁም ። እንዲያውም ፡ እስከ አራት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ባለሥራ ፡ መሆኔን ፡ ረስቸው ፡ ነበር ። በሳምንቱ ፡ ወደ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ሄድኩና ፡ «ትንሽ ፡ አሞኝ ፡ ሰንብቶ ፡ ነበር» ስል ፡ ለክፍል ፡ አለቃዬ ፡ አስታወቅሁ ። ምናልባትም ፡ ታሪኬን ፡ አስቀድሞ ፡ ሰምቶ ፡ ኖሮ ይሆናል ።

«ምንክን ፡ ነው ፡ የሚያምህ ?» ሲል ፡ ጠየቀኝ ።

«እንዲያው ፡ ሰውነቴን ፡ ነው» ስል ፡ መለስኩለት ።

«የሐኪም ፡ ወረቀት ፡ አለህ ?» ሲል ፡ መልሶ ፡ ጠየቀኝ ።

«ሐኪም ፡ ቤት ፡ አልሔድኩም»

«ታዲያ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ታሞ ፡ ሲቀር ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት» አለኝ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ በሀምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ የተወጠረው ፡ ትምክህት ፡ ተበጠሰና ፡ «ይህም ፡ ደግሞ ፡ በዛ ! ሰውኮ ፡ ሲታመም ፤ መታመሙን ፡ አስቀድሞ ፡ እያወቀ ፡ አይደለም ። ደግሞ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ እንጅ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ አሽከር ፡ አይደለሁም» ብዬው ፡ ከቢሮው ፡ ተመንጠቅሁ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ተመልሸ ፡ አልሔድኩም ። ያሀምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያልቅ ፡ መች ፡ መሰለኝ ! ግን ፡ በጤናዬ ፡ ነበርኩ ።



እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ ትርጓሜ ፡ ያላገኘሁለትና ፡ ባስታወስኩት ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ የሚገርመኝ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሰውነቴ ፡ ውስጥ ፡ ድንገት ፡ የተቀሰቀሰው ፡ ጾረ-ፍትወት ፡ ነው ። መጠጡ ፡ ይሆን ? ምግቡ ፡ ይሆን ? ሆቴል ፡ መብላት ፡ ይዤ ፡ ነበር ። ወይስ ፡ በገንዘቤ ፡ አማካይነት ፡ የፈለግኋትን ፡ ሴት ፡ ለማግኘት ፡ የምችል ፡ መሆኔ ፡ ስለታወቀኝ ? እንጃ ! ምክንያቱን ፡ በትክክል ፡ አልተረዳሁትም ። ብቻ ፡ የፍትወት ፡ ሥጋ ፡ አውሬነት ፡ ድንገት ፡ አደረብኝ ። እንስሶች ፡ እንኳ ፡ ለሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ የተወሰነ ፡ ወራትና ፡ ጊዜ ፡ አላቸው ። የኔው ፡ ግን ፡ የተለይ ፡ ነበር ። አንዷ ፡ በእግሯ ፡ ታስጐመጀኛለች ። ሌላዋ ፡ በጸጉሯ ፡ ታሳሳኛለች ። የአንዷ ፡ ሽንጥ ፡ ይማርከኛል ። የአንዷ ፡ ጥርስ ፡ ያምረኛል ። የሌላዋ ፡ ዓይኗ ፡ መልካም ፡ ነው ። ሴት ። ሴት ። ፍትወት ። ቀሚስ ፡ ያጠለቀ ፡ ገላ ፡ ባየሁ ፡ ቁጥር ፡ ሰውነቴ ፡ ይወጠራል ።

በመካከሉ ፡ አንዲት ፡ ታኑስ ፡ ገዝቸ ፡ ስለነበር ፡ ውሏችንና ፡ አዳራችን ፡ ሴት ፡ በማጓጓዝ ፡ ሆነ ። በመንገድ ፡ ዳር ቁማ ፡ አውቶቡስ ፡ የምትጠብቀውን ፡ « ይግቡ » ይዘን ፡ ሆቴል ፡ መሔድ ፡ ነው ። ባለትዳር ፡ ትሁን ፡ ልጃገረድ ፡ አላማርጥም ። ለሴት ፡ ስንል ፡ ናዝሬት ፡ ድረስ ፡ የሔድንበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። በአንድ ፡ ሌሊት ፡ ከሶስት ፡ አራት ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ የተኛሁበት ፡ ጊዜም ፡ ሞልቷል ። በአከፋፈሌ ፡ ደግሞ ፡ ለጋስ ፡ ነበርኩ ። በአንድ ፡ ሴት ፡ ቤት ፡ እመቤቷን ፡ ከደረ

ወይም ፡ ደግሞ ፡ ገብቸ ፡ ልዳራት ፡ ስጀምር «እ. እ.እ. አርፈህ ፡ ለጥ ፡ ትል ፡ እንደሆን ፡ እሽ - - - - - ዛሬ ፡ አላሰኘኝም» ስትል ፡ እንቅጩን ፡ ታረዳኛለች ። ስንጫወትም ፡ የወንድነት ፡ ኃይሌን ፡ ታደንቅልኛለች ። ራሷ ፡ ተደስታ ፡ እኔንም ፡ ለማስደሰት ፡ ትሞክራለች ። በእርሷ ፡ አስተያየት፡ ሩካቤ ፡ የሚያስነውር ፡ ተግባር ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ዓርት ወይም ፡ ምግብ ፤ የተፈጥሮ ፡ ጥየቃ ፡ አድርጋ ፡ ትቆጥረዋለች ። ጥሩ ፡ ገላ ፡ ነበራት ።

ከዚህም ፡ በተቀር ፡ ስናደድ ፡ የማብረድ ፤ ስከፋ ፤ ለምሳሌ ፡ ከወንድ ፡ ጋር ፡ ተጣልቸ ፡ ስመጣ ፤ የማጽናናትና ፡ የማደፋፈር ፤ ሳወራት ፤ ስሽልልላት ፡ ባለማሸፍ ፡ በጥሞና ፡ የማዳመጥ ፡ ስጦታ ፡ ነበራት ። ይህ ፡ በሙያዋ ፡ ያጠናችው ጥበብ ፡ ነው ? ወይስ ፡ በተፈጥሮዋ ? አላውቅም ።

ብቻ ፡ ግን ፡ የትም ፡ ስንከራተት ፤ ስሰክር ፤ ስጨፍር ውዬ ፡ አድሬ ፡ ወይም፡ ስንብቸ ፡ ዋናው ፡ ማረፊያየ፡ የርሷ ፡ አልጋ ፡ ነበር ።

«እኔስ ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ፍለጋ ፡ ልሔድ ፡ ነበር ! » ትላለች ፡ እንደዋዛ ፡ ጠፍቸ ፡ ስንብቸ ፡ ስሔድ ። ከምር ፡ አለመሆኑን ፡ ግን ፡ አነጋገሯ ፡ አይደብቅም ። እኔም ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ እልና ፡ ጨረቃ ፡ ዘምቸ ፡ የተመለስኩ ፡ ይመስል ፡ አድቬንቸሬን ፡ እተርክላታለሁ ።

« ጉደኛ ፡ ነህ » ትላለች ፡ በጥሞና ፡ አድምጣ ፡ ስት



ጨርስ ። ከዚያም ፡ «ገንዘብ ፡ አለህ ? እስቲ ፡ ትንሽ ፡ ሥጋ ልግዛ» ስትል ፡ እንደዋዛ ፡ ትጠይቀኝና ፡ መልስ ፡ ሳልሰጣት ፡ ኮቴን ፡ ታቀብለኛለች ። ስሰጣትም ፡ ለሥጋ ፡ መግዣ ብቻ ፡ አይደለም ። እንኳን ፡ ለርሷ ፡ ለሌሎችም ፡ ለጋስ ፡ ነበርኩ ።

ወደቤቴ ፡ ደግሞ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፤ ከሦስት ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በውድቅት ፡ ሌሊት ፤ ወይም ፡ በጧት ፡ ገደማ ፡ እሔድ ፡ ነበር ። ነገር፡ ግን ፡ የምሔደው ፡ ሚስቴ ፡ ወይም ፡ ልጆቼ ፡ ናፍቀውኝ ፡ እነርሱን ፡ ለመጐብኘት ፡ አልነበረም ። ልጆቼን ፡ ዓይናቸውን ፡ ካየሁት ፡ ዘመንም ፡ የለኝ ። ጧት ፡ ስመጣ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሔደው አገኛቸዋለሁ ። ሌሊት ፡ ስገባ ፡ ደግሞ ፡ ተኝተዋል ። ስጠፋና ፡ ሲጠይቁ ፡ እናታቸው ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ትሰጣቸው ኖሮ ፡ ይሆን ? አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ደክሞኝ ፡ ለማረፍ ፡ ብቻ ፡ ስፈልግ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የገዳም ፡ ሠፈሯ ፡ ልጅ ፡ ቤት ከውስጥ ፡ በኩል ፡ ተዘግቶ ፡ ሲቆየኝ — እንግዳ ፡ አለባት ፡ ማለት ፡ ነው—ወደቤት ፡ እሔዳለሁ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቴ ፡ ሠፈር ፡ ስጨፍር ፡ አድሬ ፡ ሩቅ ፡ መሔዱ ፡ ሲታክተኝ ፡ በዚያው ፡ ጐራ ፡ እላለሁ ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ «እንዲያው ፡ ጐረቤትስ ፡ ምን ፡ ይለኝ» የሚል ፡ ትዝብት ፡ ይሰማኝና ፡ እሔዳለሁ ።

እፎይታ ፣ ተሰማኝ ። በገባሁ ፣ ቁጥር ፣ ከገበታው ፣ ላይ ፣ ተቀምጦ ፣ የሚቀዘቅዘው፣ ምግብ ፤ ከወንበሩ፣ ላይ ፣ ተደፍቶ የምታንጐላቸውና ፣ ስቆጣ ፤ ስናገር ፣ አንገቷን ፣ ዝቅ ፣ አድ ርጋ ፣ የምትቀበለኝ ፣ የባለቤቴ ፣ ትርኢት ፣ መንፈሴን ፣ እያወከ ፣ አስቸግሮኝ ፣ ነበር ። አልፎ ፣ አልፎም ፣ ቢሆን ፣ ሕሊናዬ ፣ ካሠቃየኝ ፣ ጤናማ ፣ አእምሮ፣ ነበረኝ ፣ ማለት ፣ ነው ። በባለቤቴ ፣ መሔድ ፣ ግን ፣ አንዱ ፣ የሕሊና ፣ ልጓም ወለቀ ።

ከዚያ ፣ በኋላ ፣ በአራት ፣ ቀንም ፣ ሆነ ፣ በሳምንት ፣ ወደቤቴ ፣ መሔድ ፣ ፈጽሞ ፣ አላስፈለገኝም ። ከመሸበት ፣ አድራለሁ ። እንዲያም ፣ ሲል ፣ ሆቴል ፣ አርፋለሁ ። በአ ውቶሞቢል ፣ ውስጥ ፣ እንቅልፌን ፣ የተወጣሁበት ፣ ጊዜም ይኖራል ። አንድ ፣ ቀን ፣ በአጋጣሚ ፣ ሳልፍ ፣ ቤቱን ፣ ሌላ ሰው ፣ ገብቶበት ፣ አየሁ ። ዕቃውን ፣ ሌባ ፣ ዘረፈው ? ወይስ ባለቤቱ ፣ በኪራይ ፣ ያዘው ? አልጠየቅሁም ። የረባ ፣ ዕቃ ፣ አልነበረም ። ቢኖርም ፣ ያን ፣ ጊዜ ፣ ደንታ ፣ አላደረግሁም ።

አንድ ፣ ሰው ፣ ስድ ፣ ለመሆን ፣ ከፈለገና ፣ ከጀመረ ፣ የሚያግደው ፣ ነገር ፣ የለም ። በተለይም ፣ ገንዘብ ፣ ካለ ። እኔም ፣ ብዙ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ ሠርቻለሁ ። ትንሽ ፣ የብልግና አነጋገር ፣ ነው ፣ ባትሉኝ ፣ ሴቶችን ፣ አሻንጉሊቴ ፣ አድርጌ ያቸው ፣ ነበር ። እንደሴት ፣ ተታላይና ፣ ግብዝ ፣ ፍጡር ፣ አለ ? ቆንጆ ፣ ነሽ ፣ በላት ፣ ትፍነሽነሻለች ። ወደድኩሽ ፤ ሞትኩልሽ ፣ በላት ፣ ታምናለች ። ላፋምሽክን ፤ ሞዳሞቭን ፣ አሳዩት ፣ ትሽነፋለች ። የስንቶቹን ፣ ሕይወት ፣ አበላሸሁ ? በስንቶቹ ፣ ተጫወትሁ ? ስንቶቹን ፣ በዘመኑ ፣ ወንድ ፣ ላይ ተስፋ ፣ እንዲቆርጡ ፣ አደረግሁ ? ዝርዝራቸውን ፣ መዝግቤ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ በእርግጥ ፣ ሬኮርድ ፣ እሰብር ፣ ነበር ። በተለ ይም ፣ የደረሱ ፣ ልጃገረዶች ፣ ዋና ፣ አደኔ ፣ ነበሩ ። ባንድ ፣ በኩል ፣ ጭውነትና ፣ ይሉኝታ ፣ ሲሰማቸው ፣ በሌላ ፣ በኩል ፍቅር ፣ ሲጠማቸው፣ በቀላሉ ፣ ይሸነፋሉ። አንድ ፣ ሁለቴ ፣ ሮሚዮና ፣ ጁሊየትን፣ ማንበብ ፣ ነው። ሮማንቲክ፣ መምሰል ነው ። ወጥመዴ ፣ ውስጥ ፣ በቀላሉ ፣ ይገባሉ ። አንዳንዶቹ ጠንቃቆች ፣ ናቸው ። ግን ፣ ከአልጋ ፣ ለማድረስ ፣ « አገባ ሻለሁ ፤ በሞቴ ፣ እንጋባ» ይባላል ። ምናልባት ፣ የምጸጸት በት ፣ ቢኖር ፣ በራሴ ፣ በደረሰው ፣ ሳይሆን ፣ የሕይወትና ፣ የእውነተኛ፣ ፍቅር ፣ አስተያየታቸውን፣ ስላቃወስኩባቸው ፣ ስለነዚያ ፣ «ንጹሐን» ነው ። ምናልባት ፣ አንዳንዶቹ ፣ ወደ ፊት ፣ ወንድንና ፣ ፍቅር ፣ የሚባል ፣ ነገርን ፣ ላለማመን ፣ ምለው ፣ ይሆናል ። ይህ ፣ መቸም ፣ የአሁኑ ፣ ስሜቴ ፣ ነው ። ያን ፣ ጊዜ ፣ ግን ፣ ሚሊም ፣ አልተጨነቅሁበትም።

## ምዕራፍ ፣ ፩ ።

በዚህ ፣ መካከል ፤ የስድነትና ፣ የአለሌነት ፣ ኑሮዬን— ይህም ፣ በአሁኑ ፣ አስተያየቴ ፣ ነው—ደህና ፣ በምቀጭበት ፣

ታኑስ ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ብቻ ፡ የሔደች ፡ በደህና ፡ የተያዘች — አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአቶሞቢሌ ፡ ውስጥ ፡ ስለምኖርና ፡ ብዙ ፡ ልጃገረዶችም ፡ ስለማጓጉዝባት ፡ በየሰዓቱ ፡ አስወለውላትና ፡ አሳጥባት ፡ ነበር — ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ የምታወጣ ፡ ነበረች ። ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ፡ የምፈልገው፡ ገንዘቡን ፡ እጅ፡ በጅ፡ ጥሎ፡ በጥድፊያ፡ የሚገዛኝ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ምናልባት፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ባድር ፡ ኖሮ፡ በአንድ፡ ሺህ ፡ አምስት፡ መቶ፡ ብር፡ ስንኳ ፡ ሳልሸጣት ፡ አልቀር ፡ እንደነበር ፡ ይሰማኛል ። ማታ ፡ መጠጣት ፡ ነበረብኝ ። ሴት ፡ ማግኘት ፡ ነበረብኝ ። ጓደኞቼ ፡ የውሀ ፡ ሽታ ፡ ሆኑ ። አልፈርድባቸውም ። እንደኔው ፡ ገንዘባቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ሌላውን ፡ የሚያሜርሱ ፡ ነበሩ ። ከሌለኝ ፡ ምን ፡ እኔን ፡ አሳጀባቸው ? « የገንዘብ ፡ የለሾች ፡ ክበብ ፡ » አናቋቁም ። ብቻ ፡ ትንሽ ፡ የቆጨኝ ፡ ልብሴንና ፡ የቤት ፡ ዕቃዬን ፡ አለመከወኔ ፡ ነበር ። አዎ ! አሁን፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ ደህና፡ ዋጋ ፡ ያስገኝልኝ ፡ ነበር ። ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ለሦስት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ መጠጥና ፡ ሲጋራ ! ያላኖሩት ፡ እንቅርት ፡ አያገለግልም ።

ሃምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ እንዲያ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ቡን ፡ ሲል ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ብዙ ፡ አልነበረም ። ወጭ፡ ባደረግሁ ፡ ቁጥር ፡ እያወጣሁ ፡ ስቆጥረው ፡ ከፉኛ ፡ ያንስ



ብኛል ። ለምን ፡ ጊዜ ! ፡ እስቲቆይ! ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ ያን ፡ ያህል - - - ለእንጊሊት — አሥራ ፡ ሁለት ፡ ብር - - - ለሲጋራ - - - ለታክሲ - - - ምነው ፡ ገንዘቡ ፡ መቅኖ ፡ አጣ ! ! በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ ቁጠባ ፡ ልማር ፡ ሞከርኩ ። አብዛኛው ንም ፡ ጊዜ ፡ የማሳልፈው ፡ ከገዳም ፡ ሠፈሯ ፡ ልጅ ፡ ቤት ፡ ነበር ። ወድጄ ፡ አይደለም ። ግን ፡ ያለ ፡ አውቶሞቢል ፡ እንደቀድሞው ፡ ብዙም ፡ መዘዋወር ፡ አልቻልኩም ። ታክሲ ፡ የልብ ፡ አያደርስም ። ወጭውም ፡ በዚያ ፡ ልክ ፡ ነው ። አውቶሞቢል ፡ ሲኖር ፡ ያለገንዘብም ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ ለማታለል ፡ ይቻላል ። ግብዞች ! ባለአውቶሞቢል ፡ ሁሉ ፡ ጨዋ ፡ ይመስላቸዋል ! አውቶሞቢሉም ትልቅና ፡ አዲስ ፡ ሲሆን ፡ ጭውነቱ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ይከብዳል ። ገንዘቡ ፡ ለጊዜው ፡ በጣም ፡ ቢያስፈልገኝም ፡ የመኪናዬ ፡ አለመኖር ፡ በጣም ፡ በደለኝ ። ወጭዬን ፡ አልቀነሰችልኝም ።

ከአውቶሞቢሏ ፡ ሽያጭ ፡ ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ለገዳም፡ ሠፈሯ ፡ ልጅ ፡ ሰጠኋት ። ለምን ፡ እንደሰጠኋት ፡ አላውቅም። ምናልባት ፡ ወደፊት ፡ የእሷን ፡ እጅ፡ ማየቴ ፡ እንደማይቀር ፡ ተጠራጥሬ ፡ « እንጀራዬን ፡ በወንዙ ፡ ውስጥ መጣሌ » ነበርን ? ከዚያም ፡ ከአልጋ ፡ ላይ ፡ ተጋድሜ ፡ ስጠጣና ፡ ሳጤስ ፡ መዋል ፡ ሆነ ። ፖርሳዬም ፡ እየሳሳ ፡ በሄደ ፡ መጠን ፡ ድንጋጤውና ፡ ጭንቀቱ ፡ እየተሰማኝ ፡ መጠጡና ፡ ሲጋራው ፡ ባሰብኝ ። የሚጠብቀኝን ትንቢት

በአልኮል ፡ ለመርሳት ፡ ሞከርኩ ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ራሴን ፡ እስክረሣ ፡ ድረስ ፡ እሰክር ፡ ነበር ። በዚያው ፡ ጭልጥ ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ ይወስደኛል ። ብዙ ፡ አሰቃቂ ፡ ሕልሞች ፡ አያለሁ ። ስነቃም ፡ እንደገና ፡ ጠርሙዙን ፡ ማግኘት ፡ ነበረብኝ ።

አሁንም ፡ ሥዕሉ ፡ ይታየኛል ። በአልጋ ፡ ላይ ፡ የተጋደመ ፡ አንድ ፡ ሰው ፤ ከኮመዲናው ፡ ላይ ፡ ፓኬት ፡ ሲጋራና ፡ ጠርሙስ ፡ ኮኛክ ፡ ዞቪሎስ ፤ በሲጋራ ፡ ትር ኳሽ ፡ የተዝረከረከ ፡ ወለል ። አዎ ! ኑሮዬ ፡ ይህን ፡ መሳ ይ ፡ ነበር ። ግን ፡ ይህም ፡ ሥዕል ፡ ቢሆን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልቆየም ። አሁንም ፡ ገንዘቡ ፡ አለቀ ። ምንም ፡ የቀረኝ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ሥራ ፡ የለም ። ሳንቲም ፡ የለም ። የሚሸጥ ፡ ዕቃ ፡ የለም ። ጥገኝነቴ ፡ ከልጅቷ ፡ ነበር ። እርስዋም ፡ ውሎታ ፡ እየተሰማት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በመ ጠኑ ፡ ትወደኝ ፡ ኖሯ ፡ የተቻላትን ፡ ያህል ፡ ረዳችኝ ። እን ደቀድሞው ፡ በገፍ ፡ ባይሆንም ፡ ሲጋራ ፤ አረቄ ፤ ምግቤን ም ፡ የማገኘው ፡ ከርስዋ ፡ ነበር ። ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያል ተንቀባረርኩትን ፡ ያህል ፡ የሴት ፡ እጅ ፡ አይቶ ፡ መኖሩ ፡ የበለጠ ፡ ያበሳጨኝ ፡ ነበር ። መልኬንም ፡ በመስተዋት ፡ ስመለከተው ፡ ለውጡ ፡ ግልጥ ፡ ብሎ ፡ ይታዬኝ ፡ ገባ ። ፊቴ ፡ በልዟል ። ሰውነቴ ፡ ጠውልጓል ። ከንፈሬ ፡ ጥቅ ርሻ ፡ ሆኗል ። ልብሶቼ ፡ ከትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ዙቅቅ ፡ ይላሉ ፤ እጆቼ ፡ ይንዘፈዘፋሉ ። ትንፋሼ ፡ ልክ ፡ አይመታም ።



እንደማፈን ፡ ይቃጣዋል ። በሽተኛ ፡ መስያለሁ ። ራሴ ንም ፡ እጠላው ፡ ጀመር ። ጠባዬም ፡ እንዳሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ እየተብሰከሰከ ፡ በጣም ፡ ሳያውካት ፡ አልቀረም ። በቀ ላሉ ፡ መቆጣት ፡ ነው ። ደርሶ ፡ መከፋት ፡ ነው ። አረቄ ፡ ሲያሰኘኝ ፡ እቆጣለሁ ። ብላ ፡ ስትለኝ ፡ እቆጣለሁ።«ወጣ፡ እያልክ ፡ ነፋስ ፡ ተመታ ፤ ተንሸራሸር ፤ እስቲ ፡ ሥራ ፡ ፈልግ ፡ » ስትለኝ ፡ እኮረፋለሁ ። ሰው ፡ ገብቶ ፡ ሲጠጣ ፤ ሲጫወት ፡ እጠፋለሁ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ውጭ ፡ አምሽቼ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ እያዛጋሁ ፡ ስመለስ ፡ መኝታ ፡ ቤቱ ፡ ከውስጥ ፡ ተከርችሞ ፡ ቆየኝ ። አንኳኳሁ።ዝም ። ደግሜ ፡ አንኳኳሁ ፡ « ማነው ? » የሚል ፡ ድምፅ ፡ መጣ ። በኃይል ፡ አንኳኳ ሁት ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ልጅቷ ፡ በሩን ፡ ትንሽ ፡ ፈርቀቅ ፡ አድርጋ ፡ ሻሽዋን ፡ እያሠረች ፡ ወጣችና ፡ መግ ጊያውን ፡ የኋሊት ፡ ሰባ ፡ እንደአጥር ፡ ከመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ቆመች። እኔም ፡ እርሷን ፡ በጄ ፡ ወደ ፡ አንድ፡በኩል፡ገፍቼ፡ ለመግባት ፡ ስሞክር ፡ እግሯን ፡ እንፈራጣ ፡ ተከለችና፡ «ሰው፡ አለ ፡» አለች ። አሁንም ፡ እንደገና ፡ ልገፈትራት ፡ ሞከርኩ ።

«ሰው ፡ አለ ፡ ነው ፡ የምልህ ! ጤናም ፡ አልያዘህ ፡ እንዴ ? » አለች ፡ ምርር ፡ ባለ ፡ አነጋገር ።

«የምን ፡ ሰው ?» ስል ፡ ግንባሬን ፡ አኮፋትሬ ፡ በራስ ፡ ንቅናቄ ፡ ጠየቅኋት ።

«የምን ፡ ሰው ፡ ልበልህ ? ሰው ፡ ነዋ ! » ስትል ፡ መለሰች ። ችክ ፡ ስልባት ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ በቁልምጫ ፤ « ውይ፡ አየልዬ፡ ለምን፡ እንደዚህ ፡ ትሆናለህ ? » አለችና፡ በክንዴ ፡ እየመራች ፡ ወደባንኮው ፡ ወስዳ ፡ ቀንዶ ፡ ቀዳችልኝ ። ሰውየው ፡ ወጥቶ ፡ ሲሄድ ፡ እየተጎነጨሁ ፡ የጐሪጥ፡ አየሁት ። ጸጉሩ ፡ ግራጫ ፡ የመሰለ ፡ አዛውንት ፡ ነበር ። ሚስት ፡ ትኖረው ፡ ይሆን ? የበደልነው ፡ ጐልማሶች ፡ ብቻ ፡ አይደለንም ።

ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንሥቶ ፡ በኔና ፡ በልጅቱ ፡ መካከል፡ ያለው ፡ ግንኙነት — በትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ የሁለታችን ፡ አኗኗር — በጣም ፡ የተወጠረ ፡ ሆነ ። ብዙ ፡ አንጨዋወትም ። አብረን ፡ እንተኛለን ። ነገር ፡ ግን ፡ የፍቅር፡ ድሪያ ፡ አልነበረም ። ስፈልግ ፡ ፍትወቴን ፡ እንደ ፡ አመጋገብ ፡ በዝምታ ፡ አደርሳለሁ ። ሲያዛጋኝ ፤ ሲያቁነጠንጠኝ፡ መለኪያውንና ፡ ፓኬት ፡ ሲጋራውን ፡ እንደምታቀርብልኝ ፡ ሁሉ ፡ ገላዋንም ፡ ያለአንዳች ፡ ስሜት፡ ትሰጠኛለች።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ አብረን ፡ ኖርን ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ጠባይ ፡ እየባሰበት ፤ ሰውነቴም ፡ እየመነመነና ፡ እየጠወለገ ፡ ሲሄድ፤ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የርሷው ፡ ንግድ ፡ እየቀዘቀዘ ፤ ግንባሯም ፡ በይበልጥ ፡ እየተኮፋተረ ፡ ከመሄድ፡ አላቋረጠም። ራሴን ፡ ጠላሁ ። ርሷንም ፡ ጠላሁ ። ምናልባት ፡ አፍ፡



አውጥታ ፡ አልተናገረችውም ፡ እንጂ ፤ እርሷም፡ በበኩሏ፡ ራሷን ፡ ጠልታ ፡ እኔንም ፡ ጠልታ ፡ ይሆናል ። ሳይወዱና ፡ ሳይዋደዱ ፡ ባንድ ፡ የአኗኗር ፡ መረብ ፡ ውስጥ ፡ የተጠመዱ ፡ ፍጥረቶች ፡ ሆነን ፡ ነበር ።

እንድርቃት ፤ እንድወጣላት ፡ የምትፈልግ ፡ መሆኗ፡ ይሰማኛል ። ግን ፡ የት ፡ ልሂድ ? አንዱ ፡ ምርጫዬ ፡ ልመና ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ኑሮ ፡ ቢሆን ፡ በሌላ ፡ አስተያየት ፡ ከልመና ፡ የማይሻል ፡ መሆኑን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አልተገነዘብኩም ። «ብዙ ፡ ከሥሬላታለሁ ’ ኮ ፡ ይህ ፡ አይበዛብኝም ! »እያልኩ፡ ራሴን ፡ አማከርኩት ።

«አየለ፤ በዚህ፡ አኳኋን፡ እስከመቼ፡ እንዘልቀዋለን ?» አለች ፡ ከአጠገቤ ፡ አረቄ ፡ ሙሉ ፡ ብርጭቆ ፡ እያስቀመጠችልኝ ። ከዚያም ፡ በርጩሜውን ፡ ቀረብ ፡ አድርጋ ፡ ከአልጋው ፡ ግርጌ ፡ ተቀመጠች። ሁለት ፡ ቀን፡ ሙሉ፡ ፈጽሞ፡ አልተነጋገርንም፡ ነበር ። ከቤት፡ አልወጣሁም። ሊጠጣና፡ ሊጫወት ፡ የሚገባውንም ፡ ሁሉ ፡ ዓይኔን ፡ እያጕረጠረጥኩ ፡ ስመልሰው ፡ ሰንብቻለሁ ። አቀራረቧ ፡ ለቁም ፡ ነገር ፡ መሆኑ ፡ ገባኝ ። ጥያቄዋ ፡ ያልገባኝ ፡ ይመስል ፡ ፊቴን ፡ ኮስተር፡ አድርጌ ፡ በሙሉ ፡ ዓይን ፡ ተመለከትኳት።

«ለምን ፡ ትንሽ ፡ አታስብም ? » አለች ፡ እንደገና ፡ በልመና ፡ ቃል ። ራሴን ፡ አወዛወዝኩ ።

ተነሣችና ፡ ወረቀትና ፡ እርሳስ ፡ አምጥታልኝ ፡ «እስቲ ፡ ተመልከት ። የራስህን ፡ ሕይወት ፡ አበላሸህ። ደግሞ ፡

የኔን ፡ አኗኗር ፡ ለምን ፡ ታደናቅፍብኛለህ ? » ስትል ፡ በርጋታ ፡ ጠየቀችኝ ።

«ምንድን ፡ ነው ፡ የምትይው ? » አልኩና፡ ጻፍኩ ።

«መጠጥ ፡ ቤት ፡ የከፈትኩት ፡ ለጽድቅ ፡ ይመስልሃል ? ወይስ ፡ ራሴን ፡ ስነግድ ፡ እደሰትበታለሁ ?

« እሺ ፡ ታዲያ?» ፡ ስል ፡ በርሳሱ ፡ ጨነቆርኩ። ገልመጥ ፡ ብላ ፡ ጽሑፉን ፡ አነበበችና ፡ « ለመኖር ፡ ነው ። መኖር ፤ ሕይወት ፤ አስገድዶኝ ፡ ነው ። እየከፋኝ ፡ እሳሳታለሁ ። ከሚቀፈኝ ፡ ጋር ፡ እጫወታለሁ ። አብሬው ፡ እተኛለሁ ። ሌላ ፡ የኑሮ ፡ ምርጫ ፡ የለኝምና ። አየለ ! እንዴት፡ ላስረዳህ ? » አለች ። አነጋገሯ ፡ የጭንቀት ፡ ዜማ ፡ ነበረበት ።

« እ ኮ ፡ ለምን ፡ አትተይውም ? » ብዬ ፡ ጻፍኩላት ፡

«በምን ፡ እኖራለሁ ? ታሪኬን ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ነግሬህ ፡ የለም ? ከፀሐይ ፡ በታች ፡ አንድም ፡ ሁነኛ ፡ ዘመድ ፡ የለኝም ። ራሴ ፡ ብቻ ፡ ነኝ ። ራሴም ፤ ራሴን ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚችልበት ፡ ሙያ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። በኔ ፡ ሥፍራ ፡ ሆነህ፡ ብታዬው ! » ። አገጯን፡ በጁዋ ፡ አስደገፈችና ፡ አንገቷን ፡ ደፍታ ፡ ታስብ ፡ ገባች ። ምስኪን ። ምስኪኖች ። ሌላ ፡ ዕድል ፡ ስላጡ ፡ በዚያ ፡ የሴቶች ፡ ጥንታዊ ፡ ሙያ ፡ ብቻ ፡ ተሰማሩ ። ገና ፡ ወጣት ፡ ነበረች ። መልኳም ቢሆን ፡ ምንም ፡ አይልም ።



«ለምን ፡ ባል ፡ አታገቢም ? » ብዬ ፡ ጻፍኩ ። እንዴ ! አሁን ፡ እርሷ ፡ ባል ፡ አግብታ ፡ ብትሔድ ፡ ኖሮ ፡ የት ፡ እጠጋ ፡ ነበር ? የሚል ፡ ሐሳብ ፡ ደግሞ ፡ ሳይጨርፈኝ ፡ አልቀረም ።

አንገቷን ፡ እንደዋዛ ፡ ቀና ፡ አደረገችና ፡ «እኔ ፡ ነው፡ የማገባው ? ወይስ ፡ ማነው እኔን ፡ የሚያገባኝ ? » ስትል ፡ ጠየቀችኝ ።

አጐንብሳ ፡ የምጽፈውን ፡ ታነብ ፡ እንደነበር ፤ «ለምን ፡ አንጋባም?» ፡ ብዬ ፡ ጽፌ ፡ ሳልጨርስ ፡ ተንከትክታ፡ የምሬት፡ ሳቅ፡ ሳቀች።ከዚያም፡ ከተቀመጠችበት፡ ተነሣችና ፡ ራሷን ፡ እየነቀነቀች ፤ «ቂል — ፈጽሞ ፡ ቂል፡ ነህ፡ ልበል ፡ አየለ ! ወይስ ፡ ካላንተ ፡ ብልጥ ፡ ያለ ፡ አይመስልህም ? »አለችኝ ። ከኮመዲኖው ፡ ላይ ፡ ሲጋራ ፡ አነሣችና፡ አቀጣጠለች ። እንደኔም ፡ ሳይበዛ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ታጨሳለች ። ትኩር ፡ ብዬ ፡ አየኋት ። ሲጋራውን ፡ አቦነነችና ፡ ከፉኛ ፡ አስተዋለችኝ ። ከዚያም ፡ እንደገና ፡ ራሷን ፡ ነቀነቀች ።

«በተከሊል ፡ ነው ፡ በሰማንያ ? »

በማሾፍ ፡ የቁጣ ፡ መልክ ፡ አሳየሁ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ እኔም ፡ ሴቶችን ፡ እንደ ፡ አሻንጉሊት ፡ እጫወትባቸው ፡ ነበር ። የወደቀ ፡ እንጨት ፡ ሆነና ፡ ነገሩ ፡ የተገላቢጦሽ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ አሻንጉሊት ፡ እታይ ፡ ጀመር !

ቁጣዬ ፡ የተሰማት ፡ ይመስል ፡ ወዲያው፡ አነጋገሯን፡
ቀየረችና ፡ «እሽ ፤ መጋባቱን ፡ ተጋባን ። ከዚያ ፡ በኋላስ ፡
ምን ፡ እንሆናለን ? » ስትል ፡ በለዘብታ ፡ ጠየቀችኝ ።

አልመለስኩላትም።ምንም፡መልስ ፡ አልነበረኝም።እር
ሷም ፡ ቢሆን ፡ አጠያየቋ ፡ ከኔ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ አል
ነበረም ።

ለኔም ፡ ለርሷም ፡ ከአረቄው ፡ ቀዳችና ፡ ንግግሯን ፡
ቀጠለች ። « ልታስተዳድረኝ ፡ ነው ? እስቲ ፡ ራስክን ፡
ተመልከተው ። ሀብትህን ፡ ጨርሰሀል ። ከሥራ ፡ ወጥተ
ሀል ። ምንም ፡ የለህ ። ተስፋ ፡ አስቆራጭ ፡ አትበለኝና ፡
ተስፋ ፡ የለህም ። ራስክም ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠሃል ። ከኔ ፡ አት
ሻልም ። እንዲያውም ፡ እኔ ፡ ብወደውም - ብጠላውም ፡
አንድ ፡ የመስተዳደሪያ ፡ ሙያ ፡ አለኝ ። ይህ ፡ ካንተ ፡
በኩል ፡ ነው ። ከኔ ፡ በኩልስ ? እኔ ፡ ላስተዳድርህ ፡ ነው ?
ርስት ፡ አለኝ ? ሥራ ፡ አለኝ ? ወይስ ፡ ሁለታችን ፡ ልመና ፡
ልንሄድ ፡ ነው ? ተቆራኝቶ ፡ በመሠቃየት ፡ አላምንም ።
የጣለብኝን ፡ ዕድል ፡ ብቻዬን ፡ ልቋቋመው ። ዕድልህን ፡
ሞክር ። ደግሞ ፡ እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ ሀብትም ፡ ቢኖርህ
አላገባህም ፡ ነበር ። ከአብራክህ ፡ የወጡትን ፡ ልጆች ፡
የትም ፡ ያፈሰስክ ፡ እኔን ፡ ትጠብቀኛለህ ፡ ብዬ ፡ ነው ? »

በዛብኝ ። እርግጥ ፡ የተናገረችው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡
ነበር ። በቃላት ፡ የቀረበ ፡ ትክክለኛ ፡ የራሴ ፡ መስተዋት ።



ግን ፡ እርሷ ፡ ማን ፡ ሆነችና ፡ ነው ፡ ራሴን ፡ ልታሳየኝ ፡
የምትሞክር ? ከሁሉ ፡ ደግሞ ፡ ሕሊናዬን ፡ የሚቀሰቅስ
ብኝ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ያናድደኛል ። ከመቆጣቴም ፡ የተነሣ
እርሳሱን ፡ ጣልኩና ፡ «ዳ ዳ ዳ » ከሚል ፡ ድምፅ ፡ ጋር ፡
ጋር ፡ ጠረጴዛውን ፡ በቡጢ ፡ መታሁት ። በተለይ ፡ የዚህ፡
ቀን ፡ ዝርዝር ፡ ሁናቴ ፡ የሚታወሰኝ ፡ ምክንያት፡ አይገባ
ኝም ። በአእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ተቀርጾ ፡
የቀረው ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ ይመስላል ።

እንደገና ፡ አረቄ ፡ ለሁለታችንም ፡ ቀዳችና ፡ መልሳ፡
ልታስረዳኝና ፡ ልትማጠነኝ ፡ ሞከረች ። ጊዜው ፡ ድንግዝ
ግዝ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ሰዎች ፡ እያውካኩና ፡ እየተሳ
ሳቁ ፡ ከመጠጥ ፡ ቤቱ ፡ ገቡ ። እኛ ፡ የነበርነው ፡ ከመኝታ ፡
ቤት ፡ ነው ።

«ከዚህ ፡ ቤት ፡ ሰው ፡ የለም ፡ እንዴ ! » አለ ፡ አን
ደኛው ። ልጅቷ ፡ የአረቄውን ፡ ጠርሙዝ ፡ ይዛ ፡ ወጣች ።
መለኪያ ፡ ሲንቋቋ ፡ ይሰማል ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡
ተመልሳ ፡ መጣች ።

«አየለ ፡ ለምን ፡ ወጣ፡ ብለህ ፡ ነፋስ ፡ አትቀበልም ?»
አለችኝ ። ምን ፡ ማለቷ ፡ እንደሆነ ፡ ይገባኛል ። እንደሚ
ገባኝም ፡ ታውቀዋለች ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጸያፍ ፡ በሌለ
በት ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ቢሸፋፈንም ፡ አነጋገሯ፡ እንዲገባኝ፡
አድርጋ ፡ ነበር ። በጭውነት ፡ አገላለጽ ፡ አልጋውን ፡ እፈ

ሌላ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ገባ ። ወጥታ ፡ ተቀበለችው ። ጥቂት፡ ቆይታ — ምናልባትም ፡ ዋጋውን ፡ ተነጋግራ — ተመለሰች ። አሁን ፡ በቁጣ ፡ ተሹማ ፡ ነበር ።

«ትወጣልኛለህ ፡ አትወጣም !» አለች ፡ ባማረረ ፡ ትእዛዝ ። ዝም ። «አንተን'ኮ ፡ ነው ?» ። መልስ ፡ የለም ።

«አ ! አ ፡ እትዬ ! ምን ፡ ይጨማለቅብኛል ! ከሚጨማለቅበት ፡ ሄዶ ፡ አይጨማለቅም ! እኔይቱ !» ብላ ፡ ብርድ ፡ ልብሱን ፡ ከላዬ ፡ ላይ ፡ ስትገፍ ፤ እኔም ፡ ተወራጨሁና ፡ ለጥፌ ፡ ስደነባበስ ፤ ስድቡን ፡ እያደባለቀችው ፡ ወጣች ።

ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ አጫጭር ፡ ዱላ ፡ ያነገቡ ፡ ሁለት ፡ ሰላማዊ ፡ ፖሊሶች ፡ እየመራች ፡ ከተፍ ፡ አለች ። ከርሷ ፡ ልደባደብ ፡ እንደተነሣሁ ፡ ጫማዬን ፡ ሳላጠልቅ ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ተቀምጬ ፡ ነበር ።

«እርሱ ፡ ነው !» በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ሁሉ ፡ በጣቷ ፡ ለይታ ፡ አመለከተቻቸው ። ሁለቱ ፡ ፖሊሶች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩ ። እኔም ፡ አፌን ፡ አጣምሜ ፡ ሦስቱንም፡ የተቻለ ፡ ንቀት ፡ አሳየኋቸው ።

«ጌታዬ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ነዎት ። ለምን ፡ ሴት ፡ ልጅ ያስቸግራሉ ? » አለኝ ፡ በሽምግልና ፡ አንደበት ። ፈላስፋው ፡ መጣ ! አልኩ ፡ በሆዴ ። ምኑ ፡ ያውቃል ፡ ስለኔ ፡ ትልቅነት ? ምን ፡ ያውቃል ፡ ስለሁለታችን ፡ ግንኙነት ? ምን ፡ ብላ ፡ ነግራቸው ፡ ይሆን ?



«ምንም ፡ አልፈልገው ፤ ብቻ ፡ አስወጡልኝ » አለቻቸው።በዱቤ፡ ጠጥቶብኛል፡ ብላ፡ ከሳኝ፡ ነው? ወይስ፡ በዱቤ ተኝቷል ፡ ብላ ፡ ነው ? እኔስ ፡ በበኩሌ ፡ ገንዘቤን ፡ ከፍዬ የሚገባኝን ፡ ግልጋሎት ፡ አላገኘሁም ፡ ብል ፡ ኖሮስ ፡ ? የአንደበቴ ፡ መታሠር ፡ ለዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ በደለኝ ። « ዲ ዲ ዳ ዳ » ብልባቸው ፡ ይስቁብኛል ። አይገባቸውም ። ጽፌ ፡ ላስረዳቸው ፡ ብሞክር ፡ አይቀበሉኝም ። አይገባቸውም ። ወይም ፡ የማያነቡ ፡ መሐይሞች ፡ ይሆናሉ ። በአብዛኞቹ ፡ አስተያየት ፡ ከሴት ፡ ጋር ፡ የሚጣላው ፡ ሁሉ ዋጋ ፡ የለሽ ፡ ፍጡር ፡ ነው ። ነገሩማ ፡ እኔስ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ ነበረኝ ? በዓይኔ ፡ የምገድላቸው ፡ ይመስል ፡ እየገላመጥኩ ፡ ዝም ፡ አልኩ ።

«ይነሱ ፡ ጌታዬ! » ሲል ፡ አዘዘኝ ፡ አንደኛው ።

«እርስዎን ፡ ነው ፡ ሰውዬ ! »

«ሰውዬ ፡ በክብር ፡ ብትነሣ ፡ ይሻልሀል »

በንዴት ፡ ብግን ፡ አልኩ ። —— ጌታዬ ! ሰውዬ ! ይሻልሀል ! ----- ደደብ ! ብዬ ፡ በሆዴ ፡ ሰደብኩት ። ከዚያም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ያዳምጥ ፡ የነበረው ፡ ሁለተኛው ፡ ፖሊስ ፡ « ቁልምጫው ፡ እረ ፡ ምንድነው ? » አለና ፡ በክንዴ ፡ ጐተተኝ ። አልኮልና ፡ ሴት ፡ ሲጋራ ፡ ባጠቃው፡ ሰውነቴ ፡ ጥቂት ፡ ተፈራገጥኩ ። ግብግብም ፡ ልጋጠም ፡ ሞከርኩ ። ነገር ፡ ግን ፡ በቀላሉ ፡ ክንዴን ፡ ጠምዘው ፡ የፊጢኝ ፡ ያዙኝና ፡ እየገፉ ፡ አወጡኝ ።

«አሁን ፡ እስቲ ፡ ምን ፡ ትጠቀማለህ?»ስትል ፡ ከወደ
ጀርባዬ ፡ ሰማኋት ። ምክንያቱን ፡ ሳላውቀው ፡ ካለፈው ፡
ሁሉ ፡ የአሁኑ ፡ ንግግሯ ፡ ሰውነቴን ፡ አቃጠለው ። ምናል
ባት ፡ ማሸነፏና ፡ መሸነፌ ፡ ተሰምቶኝ፡ ይሆናል ። ከነርሱ ፡
ነጥቄ ፡ እርሷን ፡ ልተናነቅ ፡ ሞክሬአለሁ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡
የሆነውን ፡ ማን ፡ ፈጽሞ ፡ አላውቅም ። በሕይወቴ፡ ውስጥ፡
አንድ ፡ የጨለማ ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ቀርቷል ። ከቶ ፡ ምንም፡
ነገር ፡ የማይታየኝ ፡ ፍጹም ፡ ጨለማ . . . ።

. . . በኋላ ፡ እንደተነገረኝ ፡ ፖሊሶቹ ፡ ከቤት ፡ ገፈታ
ትረው ፡ ካስወጡኝ ፡ በኋላ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ለቀውኛል ።
ምናልባት ፡ ስደናበር ፡ ከአንድ፡ የኤሌትሪክ፡ ምሰሶ፡ ጋር ፡
ተጋጭቼ ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ ፖሊሶቹ ፡ በዚያች ፡ ዱላ ፡
ኮርኩመውኝ ፡ ኖሮ ፡ ይሆን ? በትክክል ፡ አልታወቀም ።
ብቻ ፡ ከግንባሬ ፡ ላይ ፡ ፍንከት ፡ ተገኝቷል ፡ አሉ ። የት ፡
ስንከራተት ፡ እንዳመሸሁም፡ አይታወቅም። ከምሽቱ ፡ በአ
ምስት ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ወደልጅቷ ፡ ቤት ፡ ተመልሼ ፡ እሄዳ
ለሁ ። ከዚያም ፡ ልጅቷ ፡ አንድ ፡ ገበያተኛ ፡ ሸኝታ ፡ ከአ
ልጋዋ ፡ ላይ ፡ እንደተጋደመች ፡ አገኛታለሁ ። በባንኮው ፡
ላይ ፡ ከተደረደረው ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ባዶ ፡ ጠርሙስ ፡
ጨብጬ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ እገባና ፡ ለመጮህም ፡ ሆነ ፡ ለመከ
ላከል ፡ ፋታ ፡ ሳልሰጣት ፡ ከተኛችበት ፡ ጭንቅላቷን ፡ እፈ
ጠፍጠዋለሁ ።



ምናልባት ፡ ብዙዎቹን ፡ ያስደነቃቸው ፡ ከዚህ፡ በኋላ
የሠራሁት ፡ ነው ። ልጅቷ ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ በደም ፡ እን
ደተበከለች ፡ ከኮመዲኖው ፡ ላይ ፡ የነበረችውን ፡ ትንሽ ፡
ራዲዮና ፡ አምስት ፡ ብር ፡ አንስቼ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፫ኛ ፡
ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ እሔዳለሁ ። ከዚያም ፡ ራዲዮኑንና ፡ የአ
ምስት ፡ ብር ፡ ኖት ፡ ከተረኛው፡ ፖሊስ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ አስቀ
ምጬ ፡ ጠረጴዛውን ፡ በቡጢ ፡ ዲው ፡ አደርገዋለሁ ። በመ
ጀመርያ ፡ ሰካራም ፡ መስልኳቸው ። «ዲ ፡ ዲ ፡ ዳ ፡ ዳ» እያ
ልኩ ፡ እጄን ፡ ሳወዛውዝባቸው ፡ ደግሞ ፡ የባሰውን ፡ ግራ ፡
ገባቸው ። በፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ይጠራ
ቀማል ። ሰካራሙ፤ ወፈፌው ፤ ጥጋበኛው ፤ ሌባው ፤ ሥራ፡
ፈቱ ፤ ፖሊሶች ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አያስገርማቸውም ። ሆኖም ፡
የኔው ፡ ሁናቴ ፡ በጣም ፡ አስደንቋቸዋል ። ግራ ፡ ገብ
ቷቸውና ፡ ፈዘው ፡ ሲመለከቱኝ ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የነበ
ረውን ፡ መዝገብ ፡ ስቤ ፡ «ጥሪቷ ፡ ይሄው ፡ ብቻ፡ ነው ። አስ
ቀምጡላት ። ሬሳዋንም ፡ ኑና ፡ ተረከቡኝ» ብዬ፡ እጽፋለሁ።
እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይተያያሉ ። ይሳሳቃሉ ። ገፍትረው ፡
ሊያስወጡኝ ፡ ያስባሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንዱን ፡ ፖሊስ ፡
በክንዱ ፡ ይዤ፡ስጐትተው ፤ ሊነጥቀኝ ፡ ሲቃጣ፡ ተረኛው፡
አዛዥ ፡ «ምናልባት ፡ ከአማኑኤል ፡ ያመለጠ ፡ እብድ ፡ ይመ
ስለኛል ። ይህንን ፡ ዕቃ ፡ ወደሠረቀበት ፡ ቦታ ፡ ይሔድ ፡
ይሆናልና ፡ ተከተሉት ፡» ብሎ ፡ ያዛል ። ዕብድ ፡ የሚለው፡

ቃል ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ሲጠቀስ ፡ የመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ሰካራም ፡ ከሚለው ፡ ቅጽል ፡ ገና ፡ አላለፍኩም ፡ ነበር ።

እኔ ፡ እየመራሁ ፤ ፖሊሶቹ ፡ እየተከተሉ ፡ በቀጥታ ፡ ከልጅቷ ፡ ቤት ፡ አደርሳቸዋለሁ ። ከዚያም፡ መኝታ፡ ቤቱን፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እከፍትና ፡ «ያቻትላችሁ !» ብዬ ፡ አሳያቸዋለሁ ። እንዴት ፡ ደንግጠው ፡ ይሆን ? ልጅቷ ፡ በግንባሯ ፡ ተደፍታ ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ተዘርራለች ። አንዱ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ከወለሉ ፡ ላይ ፡ ወድቋል ። አንዱ ፡ እግሯ ፡ ከአንሶላው ፡ በላይ ፡ እስከጭኗ ፡ ድረስ ፡ ተጋልጧል ። ከወጣሁ ፡ በኋላ ፡ ተፈራግጣ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ከጭንቅላቷ ፡ የሚፈሰው ፡ ደም ፡ ፍራሹን ፡ ረዝርዞ ፡ ከአልጋው ፡ ሥር ፡ ይንጠባጠባል ። ከዚያም ፡ ኮለል ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ቀጭን ፡ መሥመር ፡ በመሥራት ፡ እስከበራፉ ፡ ተጠግቷል ። በጣም ፡ አሠቃቂ ፡ ነበር ፡ አሉ ።

ግን ፡ አልሞተችም ፡ ነበር ። ገና ፡ ታቃስታለች ። ፖሊሶቹ ፡ ወዲያው ፡ ፊስካ ፡ ይነፋሉ ። መንደርተኛ ፤ ፖሊስ ፤ ወሬኛ ፡ ይሰበሰባል ። ወዲያው ፡ አላፊ ፡ መኪና ፡ ለምነው ፡ ልጅቷን ፡ ምኒልክ ፡ ሆስፒታል ፡ ሲወስዱ ፡ እኔን ፡ ጥቂት ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ በፈቃዴ ፡ ወደሔድኩበት ፡ ፖሊስ፡ ጣቢያ፡ ይመልሱኛል ። ማረፊያ ፡ ቤት ፡ እገባለሁ ። ምናልባት ፡ የሻማ ፡ ክፊል ፡ ተብዬ ፡ ተደቁሼ፡ ይሆናል ። ከግንባሬ፡ ላይ፡



ተገኘ ፡ የተባለው ፡ ፍንክት ፡ የርሱ ፡ ይሆን ? ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡ የኔው ፡ ምርመራ ፡ ሲቀጥል ፡ ልጅቱ ታክማ ፡ ከሞት ፡ ለጥቂት ፡ አመለጠች።አንድ ፡ ዓይኗ ፡ ግን፡ ፈሰሰ ። ዋና ፡ መልኳ ፡ ዓይኗ ፡ ነበር ።

ፖሊሶቹ ፡ ቃሌን ፡ በሚቀበሉበት ፡ ጊዜ ፡ ስቃያቸውን ሳያዩ ፡ እንዳልቀሩ ፡ እገምታለሁ ። «-----ስምህ?» «----የአባትህ ፡ ስም ?» «ዕድሜህ ?» አእምሮውን ፡ የሳተ ፤ በዚህ ፡ ላይ ፡ ዲዳ ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ ጅራትና ፡ ቀንጮ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ። ግን ፡ ልጅቷ ፡ በሚገባ ፡ መስክራብኛለች ። የጣቴ ፡ አሻራም ፡ በጠርሙሱ ፡ ላይ ፡ ተገኝቷል። ራዲዮው ፤ አምስቱ ፡ ብር ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ኤግዚቢት ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ ከቤት ፡ ገፍትረው ፡ ያስወጡኝ ፡ ፖሊሶች፡እንደዚሁ ፡ ቃላቸውን ፡ ሰጥተዋል ። ወንጀሉን ፡ ለመፈጸሜ ፤ በቂ ፡ የሞቲቭ ፤ የቴክኒክና ፡ የሁናቴ ፡ ማስረጃ ፡ ነበር ። ለወንጀለኛነቴ ፡ ዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ በመቶ፡ እርግጠኞች፡ ሆነዋል።

«ጥፋተኛ ፡ ነህ ? አይደለህም ?» በአንድ፡ ተከሳሽ፡ ላይ ፍርድ ፡ ከመሰ ጠቱ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ይቀርብለታል ። ተከሳሹ ፡ ጥያቄውን ፡ በተስተካከለ ፡ አእምሮ ፡ መመለስ ፡ አለበት ። እኔም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቤ ፡ በተከሳሽ ፡ ሳጥን ፡ ውስጥ ፡ ገብቼ ፡ ተጠይቄአለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ በኩል አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወንጀለኛነቴን ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ይዞ ፡ ሲቀርብ ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ መንግሥት ፡ ለኔ ፡ ያቆመልኝ ፡ ጠበቃ ፡ ፍርዴን ፡ ለመስማት ፡

ውስጥ ፡ ተቀርጾ ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚያወሩት ፡ ስለርሱ ፡
ነው ። ከመኝታቸው ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፤ መተኮሻው ፡ የተሰ
ካባቸው ፡ ይመስል ፡ ጆሮ ፡ ግንዳቸውን ፡ ይዘው ፡ ያቃስ
ታሉ ። አውቆ ፡ አብዶቹ ፡ ደግሞ ፡ እንዴ ፡ ሲያቀምሱዋ
ቸው ፡ ይናዘዛሉ ፡ ይባላል ። የኤሌትሪኩ ፡ ትኩሳት ፡ በሽ
ታቸውን ፡ ያባሰባቸውም ፡ አይጠፋም ። የለመነው ፤ ያለ
ቀሰው ፤ የተንገበገበው ፡ ሁሉ ፡ አይቀርለትም ፡ ነበር ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ አጠያየቄ ፡ ልመና ፡
ሳይሆን ፡ በጥሞና ፡ የቀረበ ፡ ምክርና ፡ ማስጠንቀቂያ ፡
ቅምር ፡ መሆኑን ፡ ዶክተሩ ፡ በመገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ጤን
ነቴን ፡ በማስተዋሉ ፡ ይሁን ፡ እንጃ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የኤ
ሌትሪኩ ፡ ትኩሳት ፡ አልነካኝም ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ከመ
ኝታ ፡ ክፍላችን ፡ ተሰ ብስበን ፡ ስንጫወት ፡ አንዱ ፡ በሽ
ተኛ ፡ መጥቶ ፡ ሰው ፡ ይፈልግሃል ፡ አለኝ ። በጥያቄ ፡
መልክ ፡ ራሴን ፡ ነቀነቅሁ ። «አንዲት ፡ ሴትዮ ፡ ናቸው ፡»
አለ ። አ ! ሴት ! ሴት ? የምን ፡ ሴት ? የማን ፡ ሴትዮ ?
በእጁ ፡ ይዞው ፡ የነበረውን ፡ የካርታ ፡ ወረቀት ፡ ከአል
ጋው ፡ ላይ ፡ ዘረገፍኩና ፡ ወጣሁ ። ያስጠራችኝ ፡
ሴት — ቀን ፡ ቆጠራውን ፡ ረሳሁት ፡ እንጂ — አንድ ፡
ጊዜ ፡ ቤቱን ፡ ዘግታ ፡ ጥላኝ ፡ የሔደችው ፡ ባለቤቴ ፡ ነበ
ረች ። የእንጀራ ፡ ሳሕን ፡ እንደታቀፈች ፡ ወደኔ ፡ ቀረበ



ችና ፤ « እንደምን ፡ ሰነበትክ ? ሐኪሙ ፡ በጣም ፡ ተሽ
ሎታል ፡ አለኝ ። አልተገናኘንም ፡ እንጂ ፡ ሁል ፡ ጊዜኮ ፡
እመጣለሁ » አለች ፡ አንገቷን ፡ ደፋ ፡ አድርጋ፡ በጣም፡
በለሰለሰ ፡ አንደበት ። «ታዲያ ፡ ምን ፡ ይጠበስ ?» አልኩ፡
በሆዴ ። ቁጣ ፡ ሳይሆን ፡ ስሜቴ ፡ የኃፍረት ፡ ነበር ።
ለምን ፡ መጣች ? ሕሊናዬን ፡ ለመኰርኰር ፡ ነው ? ለብዙ
ጊዜ ፡ ያህል ፡ እንደዚሁ ፡ ቆምን ። በሙሉ ፡ ዓይን ፡ ለዓ
ይን ፡ ስንኳ ፡ አልተያየንም።በመጨረሻ ፡ ሳሕኑን፡ ሰጥታ፡
ተሰናብታኝ ፡ ሔደች ። ሳሕኑን ፡ ይዤ ፡ ወደክፍሌ ፡
ስገባ ፡ ሰሞኑን ፡ ሲከነክነኝ ፡ የሰነበተው ፡ እንቆቅልሽ ፡
ተፈታልኝ ። ከሦስት ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፤ ከአራት ፡
ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የቤት ፡ ምግብ ፡ በሳሕን ፡ ይመጣል
ኛል ። ከየት ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም ፡ ነበር ። ብቻ ፡ ዘበ
ኛው ፡ ስሜን ፡ ይጠራና ፡ ይሰጠኛል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡
የቤት ፡ ምግብ ፡ የሚመጣላቸው ፡ በሽተኞች ፡ በጣም ፡
ጥቂቶች ፡ ናቸው ። በዚያ ፡ መናኛ ፡ እንጀራና ፡ ዝብጥብጥ
ወጥ ፡ መካከል ፤ ዘወትርም ፡ ባይሆን፡ ክሽን፡ ያለች፡ ወጥ ፤
የነጭ ፡ ጤፍ ፡ እንጀራ ፡ ምግብ ፡ በሳሕን ፡ የሚደርሰው ፡
በሽተኛ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የሚታየው ።
እኔም ፡ በዚሁ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አፍርቻበት ፡ ነበር ።
ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ማን ፡ እንደሚልክልኝ ፡ አላ
ውቅም ፡ ነበር ። ዘበኛውንም ፡ አልጠየቅሁትም ።
ማንበብ ፡ አይችልም ። « ለካ ፡ እሷ ፡ ናት ! » ፡ አልኩ ፡

ከነርሱ ፡ መካከል ፡ የከረመ ፡ ጤነኛ ፡ ባሙቱ ፡ ራሱ ፡ ታሞ ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

እኔም ፡ በተሻለ ፡ አእምሮ ፡ ይህንን ፡ ክፍል ፡ ለመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ ስመለከት ፡ ክፉኛ ፡ ሳልደነግጥ ፡ አልቀረሁም ፡ ነበር ። ሰው ፡ መሆንን ፡ ያስጠላል ። ክቡሩ ፡ ሰው፡ እንደዚህ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ?

በፊቷ ፡ እንደተረዳሁት፡ ከጉብኝቱ፡ በተለይ፡ ልቧን፡ የነካው ፡ የሴቶች ፡ ክፍል ፡ ይመስለኛል ። ሴት ፡ በመሆኗ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ይህ ፡ ክፍል ፡ በተለይ ፡ ኀዘን ፡ የሰፈነበት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ « ሸዋዬ ፡ አንቺ ፡ ሸዋዬ ? » እያለች ፡ እንደቅዠት ፡ ልጇዋን ፡ ስትጣራ ፡ የምትኖረው፡ በሽተኛ ፡ የማንንም ፡ ልብ ፡ ትነካለች ።

አንዷ ፡ በሽተኛ ፡ « ሻሼን ፡ ነጠቁኝ , እኮ » ፡ ብላ ፡ እንደዋዛ ፡ ብታዋያት ፡ ጸጉሯን ፡ ያሰረችበትን ፡ ሻሽ ፡ ፈትታ ፡ ሰጠቻት ። ጉብኝቱ ፡ ሲጨረስ ፡ እንደማቃሠት ፡ ያህል ፡ በከባዱ ፡ ተነፈሰች ። ጉብኝቱ ፡ ስሜቷን ፡ ክፉኛ ፡ አሰቃይቶት ፡ ነበር ።

ከዚያ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ የኔንም ፡ ክፍል ፡ ገብታ ፡ አረገጠችም ። ከውጭ ፡ ሆና ፡ ታስጠራኛለች ። ከዚያም ፡ በግቢው ፤ ወደታችኛው ፡ ሠፈር ፡ ሳንወርድ ፡ ጥቂት ፡ እንንሸራሸራለን ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኔ ፡ ጤንነት ፡ ለፈተና ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ። ወደሦስተኛው ፡ ደረጃ ፡ የተዛወሩ ፡ የአእምሮ፡ በሽ



ተኞች ፡ ሁሉ ፡ የዕለት ፡ እንቅስቃሴያቸው ፤ አድራጎታቸው ፤ ንግግራቸው ፤ የፊት ፡ ገለጣቸው ፡ የቅርብ ፡ ቁጥጥር ይደረግበታል ። ዘበኞቹ ፡ ቤት ፡ ጠራጊዎቹ ፤ አልጋ ፡ አንጣፊዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ለዋናው ፡ ዶክተር ፡ በእያንዳንዱ ፡ በሽተኛ ፡ ላይ ፡ ሪፖርት ፡ ያቀርባሉ ። ከዚህም ፡ በተቀር ፡ በተለይ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የተመደቡት ፡ የሶሺያል ፡ አገልግሎት ሠራተኞች ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ ሠራተኞች — በሆስፒታሉ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ አንዲት ፡ ሴትና ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ናቸው — ዋናው ፡ ተግባራቸው ፡ ገመምተኛው ፡ ወደማኅበራዊ፡ ኑሮ ፡ እንደገና ፡ ለመግባት፡ የሚያስችለውን፡ ምክር፡ መስጠት፡ ሲሆን ፤ በሌላው፡ በኩል፡ ደግሞ፡ ከሐኪም፡ ቤቱ፡ ለመውጣት ፡ የበቃ ፡ መሆኑንና ፡ አለመሆኑን ፡ ይመረምራሉ ። ከውጭ ፡ ዘመድ ፤ አዝማድ ፤ ቤተ ፡ ሰብ ፤ ይጠይቃሉ ። ከውስጥ ፡ በሽተኛውን ፡ እንደዋዛ ፡ እያጫወቱ ፡ ሁናቴውን ፡ ይመዘግባሉ ። አንዳንዱ ፡ በሽተኛ ፤ ከእነጋገር ፡ እንዳይስት ፡ በመጠንቀቅ ፡ ዝምታ ፡ አብዝቶ ፡ ፈተናውን ፡ ይወድቃል ። ሌላው ፡ ጮሌነቱን ፡ ለማሳየት ፡ ሲቀባጥር ፡ አለመዳኑን ፡ ይገልጣል ። በሦስተኛውም ፡ ደረጃ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ የቆዩ ፡ በሽተኞች ፡ አሉ ። አንዱ ፡ ሊያመልጥ ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው፡ በአንዲት ፡ ስሕተት፡ ይወድቃል። ሌላው ፡ እየቆየ ፡ በሽታው ፡ ያገረሸበትና፡ ወደሁለተኛው፡ ደረጃ ፡ የሚዛወር ፡ አለ ። ብዙዎቹ ፡ በሽተኞች ፡ የሚታይባቸው ፡ አንዱ ፡ ትልቅ ፡ ጉድለት ፡ የውጪኛውን ፡ ኅብረ

